## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦገስት 11-20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ እና

# ከኦገስት 21-31፣ ከሴፕቴምበር 1-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ


ኦገስት 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ59 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡

በተጨማሪም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 51.3-98.3 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ሂርና 53.2፣ 98.3፣ ፣ ነቀምት፣ 89.3፣ ጊምቢ፣ 77.3፣ ዳንግላ፣ 74፣ ደብረ ሲና 63.5፣ ደብረ ታቦር፣ 63.0፣ መተማ 61.7፣ አዳማ 60.5፣ መሃልሜዳ 60.4፣ አሳሳ 60፣ ቅዳሜ ገበያ 58.4፣ 52.6፣ ሰቆጣ 54.3፣ ቴፒ 51.3፣ ይገኙበታል ፡፡





ምስል1:ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ ዋግህምራ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-250 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ በአብዛኛው መደበኛ እና ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የተመዘፈበ ሲሆን፤ በመካከለኛዉና ደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች እና የአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ኦገሰት 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ኦገሰት 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ኦገሰት 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀ

### 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የተስፋፋ የእርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በሚያዝያና ግንቦት ተዘርተው በመካከለኛና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች (እንደ ማሽላና በቆሎ) ለመሳሰሉት እንዲሁም በቅርብ ጊዜ ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉት እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 4)። በሌላ በኩል ከመኸሩ ዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ በደሴ ዙሪያ ወረዳ 012 እና 041 ቀበሌዎች የፌንጣ ክስተት የተስተዋለ ሲሆን ተባዩ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ አርሶ አደሮች ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር በመቀናጀት አፋጣኝ የመከላከል እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛሉ፡፡

### 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በአባይ፣ ተከዜ፣ በላይኛውና በመካከለኛው በባሮ አኮቦና ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው አዋሽ፣ በገናሌ ዳዋ እና በዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ሽፋን ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የወንዞችን ፍሰት እንዲጨምር፣ የግድቦችን የውሃ ክምችት እንዲያሻሽል እንዲሁም በተፋሰሶች ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ የውሃ ማከማቻዎች በቂ የውሃ መጠን እንዲይዙ ከማድረጉም በተጨማሪ የከርሰ ምድር የውሃ መጠንም ሆነ የመስኖና የሃይል ማመንጫ ግድቦች ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

Ethiopian Meteorology Institute


## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በኦገስት የመጨረሻው አሥራ አንድ ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አህዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፉ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም፣ በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፤ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7) ፡፡ ይሁን እንጂ በሰሜን፤ ሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ አከባቢዎች ተደጋጋሚነት ያለው ደረቅ ቀናቶች ይኖራሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ እና የምዕራብ ጉጂ ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም እናየአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካካለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ በላይ) |
| አፋር | የአዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | አብዛኛው የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት ሶስተኛው አስራ ቀናት ከሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊ ዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ26 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 21-31, 2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ቢኖራቸው ከሰሜን ምስራቅ አከባቢዎች ላይ እየተዳከሙ የሚሄድበት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም የክረምቱ ዝናብ በስርጭትም ሆነ በመጠን ከምስራቅ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት የሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 2)፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሀ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኦገስት አስራ አንድ ቀናት፣ በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖር ይጠበቃል። ስለሆነም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚገኙትን ዕድሎች በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን በቅድመ ዝግጅትና በተቀናጀ ክትትል ለመቀነስ ከታች የተዘረዘሩት ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦችን ማከናወን ያስፈልጋል (ሠንጠረዥ 3)፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፤ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ ፣ሁሉም የሸዋ ዞኖች ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ፣ አዊ ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | ➢ ለአፈር ዉስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት እና ለከተማ ግብርና እንዲሁም<br>➢ ለአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ እና ለአረንጓዴ አሻራ መረሃ ግብሮች | ➢ የእርጥበት መብዛት፣ የማሳዎች መጨቅየት እና ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በማሳዎች ላይ መተኛት<br>➢ ውሃገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት<br>➢ የበረዶ ክስተት | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ የአፈር መሸርሸር መከላከል ስራዎችን በስፋት መስራት<br>➢ የመሬት መንሸራተት ተጋላጭነትን መቀነስ<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>➢ አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ ፣ ምዕራብ ጉጂ ፣ ዋግህምራ፣ ደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ አዉሲ፣ ማሂ፣ ሀሪ ፣ ጋቢ ፣ አብዛኛው የሲዳማ የክልሉ ዞኖች ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | ➢ የዝናብ መቆራረጥና ደረቅ ሰሞናት መኖር<br>➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የሰብል በሽታ መከሰት፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና<br>➢ ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ የአፈርና ውሃ እቀባ ስራን አስቀድሞ ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤ |

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • አብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ተከዜ፣ መረብ በላኛዉና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ በላኛዉ የገናሌ ዳዋ | • የገጸ ምድርና የወንዞች ውሃ መጠን መጨመር።<br>• የከርሰ ምድር ውሃ መሙላት መሻሻል።<br>• የግድቦች የውሃ ክምችት መጨመር።<br>• የመስኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል።<br>• የውሃ ሀብት ተደራሽነትና የአካባቢ ኢኮኖሚ መሻሻ | • ቅፅበታዊ ጎረፍ መከሰት<br>• የደለል ስጋት መጨመር<br>• የውሃ ማፋሰሻ ቱቦዎች በቆሻሻ መዘጋት | • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የመጠጥ ውሃን አክሞ መጠቀም<br>• ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል<br>• የፍሳሽ መውረጃ ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፈ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • ታችኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ ላይኛው ዋቢ ባሮ አኮቦ ሸበሌ ተፋሰሶች | • የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል<br>• የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ከፍተኛ ትነት<br>• ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች መጠነኛ የውሃ እጥረት | • የሚገኘውን የዝናበ ውኃ አክሞ መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከላከል |
| **ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ መካከለኛና ታችኛው ዋቤ ሸበሌ ገናሌ ዳዋ፣ ተፋሰሶች | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣<br>• የወንዞች የውሃ ፍሰት መቀነስ<br>• የግድቦች የውሃ ክምችት መቀነስ<br>• የአፈር እርጥበት መቀነስ<br>• የውሃ ሀብት መጠን መቀነስ | • የገጸ ምድር የትነት መጠን መጨር | • የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |